206

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤትን
# የ1996 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ
# የተዘጋጀ አጭር ዘገባ

አዘጋጅ፡-
የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት

ሐምሌ 1996

## 1. መግቢያ

የአንድን አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠንና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ የልማት ዕቅዶችንና ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

የተዘጋጁ ዕቅዶችና ፖሊሲዎች በተግባር ላይ ሲውሉ የሚያስገኙትን ውጤት ለመከታተልና ለመገምገም እንዲቻልም በስርዓትና በሳይንሳዊ መንገድ የተሰበሰቡና የተቀነባበሩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችና የጥናት ውጤቶች ተፈላጊነት ዕሙን ነው።

ይህንን እጅግ አስፈላጊ የሆነ ተግባር ከመፈፀም አኳያ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ዓለም አቀፍ የስታቲስቲክስ አሰራር መርሆዎችን መሠረት በማድረግና የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በርካታ ጥናቶችን ከዳር በማድረስ ረገድ ውጤታማነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል። በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በሥነ-ህዝብ መስኮች አጠቃላይ ቆጠራዎችንና የናሙና ጥናቶችን አካሂዶ ለተጠቃሚዎች በማቅረቡም በሀገሪቱ ውስጥ የነበረውን የመረጃ ክፍተት ደረጃ በደረጃ በመቅረፍ ላይ ይገኛል።

## 2. የባለሥልጣኑ ዓላማ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ዓላማ፣ በቆጠራ፣ በናሙና ጥናት፣ በምዝገባና በአስተዳደራዊ መዛግብት የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚና የዲሞግራፊ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በተቀናጀ አሰራር ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ነው።

## 3. የ1996 አበይት ክንውኖች

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በ1996ዓ.ም የበጀት ዓመት የመንግስትን የልማትና የዕድገት አቅጣጫ ግምት ውስጥ በማስገባትና የመ/ቤቱን የመፈፀም አቅም በመገምገም ቅድሚያ ሰጥቶ ካከናወናቸው ዋና ዋና የጥናት ተግባራት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

መ/ቤቱ በ1996 ዓ.ም የበጀት አመት ላካሄዳቸው የተለያዩ ጥናቶች ማስፈፀሚያ 35.2 ሚሊዮን ብር የካፒታል በጀት እና ለመደበኛ ወጪዎች መሸፈኛ 14.9 ሚሊዮን ብር በድምሩ 50.1 ሚሊዮን ብር ከመንግሥት ተፈቅዶለት በሥራ ላይ አውሏል።

በዚህ መሠረት፣

*1/ የተፈጥሮ ሀብትና የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት*

- የ1996 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ውጤት ሪፖርቱ ተጠናቅሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።
- የ1996 ዓ.ም ዋናው መኸር ወቅት የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን መረጃ ውጤት ቅንብር ተጠናቆና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።
- በሶማሌ ብሔራዊ ክልል በአርብቶ አደር አካባቢዎች በአውሮፕላንና በ Conventional ዘዴ የተከናወነው የቆጠራ ውጤትና በ1996 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት የተሰበሰበው መረጃ ውጤት በአንድነት ተዘጋጅቶ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።
- በአፋር ብሔራዊ ክልል የተከናወነው የቤት እንስሳት ቆጠራ ውጤትና የ1996 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት የቤት እንስሳት መረጃ በአንድነት ተዘጋጅቶ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።
- በ1994 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በአገር አቀፍ ደረጃ በተካሄደው የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የተገኘው ውጤት ይፋ ሆኗል። ከዚህ የግብርና ናሙና ቆጠራ የተገኘው ውጤትም በ39 ጥራዞች በመጽሔት መልክ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን በውስጡም፡- በሰብል የተያዘ መሬት ስፋት፣ የመሬት አጠቃቀም፣ ልዩ ልዩ የግብርና ግብአቶች፣ የእርሻ መሣሪያዎች፣ የሰብል ማከማቻዎች፣ ዶሮና ንብ የያዙ ቀፎዎችን ጨምሮ ልዩ ልዩ የቤት እንስሳት መረጃዎችን እንዲሁም በፆታ ረገድ ሴቶች በግብርናው ዘርፍ ያላቸውን ድርሻ አካቶ ይዟል።

*2/ የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት*

- የገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት ከታህሳስ ወር 1995 ዓ/ም - የካቲት 1996 ዓ/ም ያለው መረጃ በሪፖርት መልክ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል ።

- በ106 ከተማዎች በሚገኙና በተመረጡ 119 ገበያዎች የተካሄደው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከሚያዝያ 1995 ዓ/ም እስከ መጋቢት 1996 ዓ/ም ያለው መረጃ በሪፖርት መልክ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል ።

- የ11 ክልሎች /መስተዳድሮች/ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁት የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዞች እስከ ሰኔ 1996 ዓ/ም ላሉት ወራት ስሌቱ ተከናውኖና ታትሞ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝም እስከ ሰኔ ወር 1995 ዓ/ም ድረስ ያለው ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል ።

*3/ በኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ፋይናንስ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት ዘርፍ*

- በ1995 በሚያዝያ እና ግንቦት ወራት ላይ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1994 በጀት ዓመትን የሚመለከተው የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመረጃ ቅንብርና ትንተና ሥራ ተጠናቆና ሪፖርቱ ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል ።

- የ1995 በጀት ዓመትን የሚመለከተው የትላልቅና የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመረጃ መሰብሰብ ሥራ ተጠናቋል ።

- የ1994 በጀት ዓመትን የሚመለከተው የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃ የሰንጠረዥ ቅንብርና ትንተና ሥራ ተከናውኖና ሪፖርቱ ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል ።

- በ1995 በጀት ዓመት ላይ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ውጤት ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።
- በ1995 በጀት ዓመት ላይ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ውጤት ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።
- በ1996 በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ/ምዝገባ የመረጃ መሰብሰብ ሥራ ተጠናቋል።
- በ1995 በጀት ዓመት ላይ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀለት የአከፋፋይ/የጅምላና ችርቻሮ ንግድ/ እንዲሁም የአገልግሎት ሰጪ ንግድ ጥናት ውጤት ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

*4/ የማሕበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት፣*

- የ1996ዓ.ም የመጀመሪያው ዙር የከተማ ተከታታይ የሥራ ሥምሪት ጥናት መረጃው ተሰብስቦ ተቀናብሮና ሪፖርቱ ታትሞ ለመረጃ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

*5/ ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት፣*

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች በሰበሰባቸው መረጃዎች ላይ ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር ለማድረግ የሚሹ ወገኖችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የጥሬ መረጃ (Raw Data) አሰጣጥ መመሪያ ፀድቆ በሥራ ላይ ውሏል።
- የ1995 ዓ/ም የስታቲስቲክስ አመታዊ መፅሔት (STATISTICAL ABSTRACT OF ETHIOPIA) ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል ። ከአካተታቸው መረጃዎች መካከልም፣ የሥነ ህዝብ፣ የግብርና፣ የማዕድን ምርት፣ የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የህንፃ ሥራ ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ፣

የውጭ ንግድ፣ ዓመታዊ የሀገር ሃብት፣ የመንግሥት ገንዘብ (Public Finance)፣ የመድህን (ኢንሹራንስ)፣ የጤና እና የትምህርት፣ የህግና ደንብ ፣ የስፖርትና ሲኒማ መረጃዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በዚሁ በጀት አመት በጠቅላላው 23,098 የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የሥነ ህዝብ ጥናት የጥናት ሪፖርት ቅጂዎች ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል። ከዚህም ውስጥ 19,703 ቅጅዎች ለመረጃ ተጠቃሚዎች በነፃ የተሰራጩ ሲሆን፣ 3,395 ቅጅዎች ደግሞ በብር 98,813.85 /ዘጠና ስምንት ሺህ ስምንት መቶ አሥራ ሦስት ብር ከሰማንያ አምስት ሣንቲም/ በመሸጥ የሪፖርቶች ሥርጭት ተከናውኗል።

# ተጨማሪ መረጃዎችን የያዙ አባሪዎች

# በ1996 ዓ.ም የአገሪቱ የእንስሳት ሀብት ብዛት

| ተ.ቁ | የቤት እንስሳት ዓይነት | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የዳልጋ ከብት /Cattle/ | 16,860,266 | 21,242,416 | 38,102,682 |
| 2 | በጎች /Sheeps/ | 4,116,478 | 12,459,015 | 16,575,493 |
| 3 | ፍየሎች/ /Goats/ | 4,102,149 | 9,732,553 | 13,834,703 |
| 4 | ፈረሶች /Horses/ | 702,743 | 744,531 | 1,447,274 |
| 5 | አህዮች /Asses/ | 1,761,793 | 2,008,079 | 3,769,871 |
| 6 | በቅሎዎች /Mules/ | 156,582 | 164,757 | 321,339 |
| 7 | ግመሎች /Camels/ | 176,919 | 294,226 | 471,145 |
| 8 | ዶሮ /Poultry/ | - | - | 35,656,385 |
| 9 | *የንብ ቀፎ /Bee hives/* | | | |
| | **የቀፎ ዓይነት** | **ብዛት** | | |
| | ባህላዊ | 4,205,824 | | |
| | የሽግግር | 15,341 | | |
| | ዘመናዊ | 7,448 | | |
| | ጠቅላላ | 4,228,612 | | |

ምንጭ/ *Source* -

* ማ.ስ.ባ. የ1996 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት መረጃ

## ሠንጠረዥ 1 – በኢትዮጵያ የታረሰ መሬት ስፋትና የተመረተ ምርት መጠን በሰብል ዓይነት (1996 ዓ.ም)

ኢትዮጵያ

| ሰብል | የባለይዞታ ብዛት | የታረሰ መሬት ስፋት | ምርት በኩንታል | ምርታማነት በሄክታር |
|---|---|---|---|---|
| እህል | 9,871,397 | 8,669,295 | 103,564,132 | |
| ብርዕና አገዳ | 9,628,505 | 6,998,977 | 90,062,375 | |
| ጤፍ | 4,562,933 | 1,989,068 | 16,773,480 | 8.43 |
| ገብስ | 3,473,903 | 920,127 | 10,796,861 | 11.73 |
| ስንዴ | 3,380,343 | 1,098,907 | 16,144,412 | 14.69 |
| በቆሎ | 6,299,746 | 1,367,115 | 25,429,653 | 18.6 |
| ማሽላ | 3,636,444 | 1,283,654 | 17,424,536 | 13.57 |
| ዳጉሳ | 1,053,159 | 304,758 | 3,051,014 | 10.01 |
| አጃ | 256,657 | 30,048 | 387,337 | 12.89 |
| ሩዝ | 25,426 | * | * | * |
| ጥራጥሬ | 5,308,211 | 1,099,535 | 10,373,131 | |
| ባቄላ | 2,897,531 | 381,988 | 4,268,917 | 11.18 |
| አተር | 1,345,129 | 211,564 | 1,703,653 | 8.05 |
| ሽምብራ | 1,806,257 | 183,752 | 1,721,529 | 9.37 |
| ሽንብራ | 622,350 | 154,281 | 1,359,299 | 8.81 |
| ምሥር | 468,270 | 52,062 | 352,748 | 6.78 |
| ጓያ | 409,233 | 82,713 | 789,545 | 9.55 |
| አኩሪ አተር | 14,171 | 1,027 | 4,574 | 4.46 |
| አብሽ | 429,490 | 17,133 | 124,540 | 7.27 |
| ግብጦ | 86,216 | 15,016 | 48,326 | 3.22 |
| የቅባት እህሎች | 2,445,750 | 570,783 | 3,128,626 | |
| ኑግ | 936,804 | 281,718 | 1,189,950 | 4.22 |
| ተልባ | 878,339 | 142,899 | 773,634 | 5.41 |
| ለውዝ | 125,278 | 20,217 | 207,150 | 10.25 |
| ሱፍ | 146,740 | 8,401 | 50,427 | 6 |
| ሰሊጥ | 318,801 | 91,527 | 614,621 | 6.72 |
| ጎመን ዘር | 579,495 | 26,021 | 292,844 | 11.25 |
| አትክልት | 3,831,083 | 82,333 | 3,879,469 | |
| ሰላጣ | 22,408 | 130 | * | * |
| ጥቅል ጎመን | 138,330 | 1,843 | 85,776 | 46.54 |
| አበሻ ጎመን | 2,229,904 | 22,377 | 2,135,915 | 95.45 |
| ቲማቲም | 107,509 | 3,761 | 548,707 | 145.9 |
| ቃሪያ | 594,556 | 4,471 | 413,870 | 92.57 |
| በርበሬ | 1,302,534 | 49,611 | 669,078 | 13.49 |
| ቆስጣ | 42,465 | 140 | 10,746 | 76.57 |
| ሥራ ሥር | 3,841,212 | 158,731 | 16,055,245 | |
| ቀይ ሥር | 178,991 | 1,216 | 140,955 | 115.88 |
| ካሮት | 84,325 | 1,108 | 100,232 | 90.48 |
| ሽንኩርት | 786,860 | 17,017 | 2,166,893 | 127.34 |
| ድንች | 1,150,645 | 54,603 | 5,097,150 | 93.35 |
| ነጭ ሽንኩርት | 1,070,549 | 9,465 | 1,353,939 | 143.05 |
| ጎደሬ | 886,972 | 28,380 | 2,224,646 | 78.39 |
| ስኳር ድንች | 1,022,185 | 46,942 | 4,971,428 | 105.91 |
| ፍራፍሬ | 1,952,158 | 44,338 | 2,495,902 | |
| አቡካዶ | 391,775 | 2,938 | 172,007 | 58.54 |
| ሙዝ | 1,293,155 | 29,083 | 1,751,497 | 60.22 |
| ዘይቱና | 134,700 | 1,063 | 11,942 | 11.23 |
| ሎሚ | 114,755 | 735 | 9,661 | 13.15 |
| ማንጎ | 350,067 | 4,964 | 292,283 | 58.88 |
| ብርትኳን | 303,886 | 2,533 | 126,118 | 49.78 |
| ፓፓዬ | 376,678 | 2,371 | 132,039 | 55.68 |
| አናናስ | 21,862 | * | * | * |
| ጫት | 1,731,224 | 111,578 | 933,398 | 8.37 |
| ቡና | 2,420,827 | 232,439 | 1,261,880 | 5.43 |
| ጌሾ | 1,472,524 | 20,792 | 249,204 | 11.99 |
| ሸንኮራ አገዳ | 717,718 | 14,292 | 997,600 | 69.8 |

ምንጭ:- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን የ1996 መኸር ናሙና ጥናት

# የ1996 ዓ.ም የመጀመሪያ ዙር የከተማ ተከታታይ የሥራ ሥምሪት ጥናት አጠቃላይ አመልካች ውጤቶች በፆታ

| አመልካች/Indicators | ፆታ | | |
|---|---|---|---|
| | ድምር | ወንድ | ሴት |
| የሀገሪቱ ጠቅላላ የከተሞች ሕዝብ ብዛት | 8,541,124 | 4,083,933 | 4,457,191 |
| ዕድሜያቸው አስር እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሕዝብ ብዛት | 6,676,324 | 3,140,888 | 3,535,436 |
| ለምርታማ ሥራ ስምሪት ተሳትፎ ብቁ የሆነ የሰው ኃይል | 3,868,400 | 1,974,424 | 1,893,976 |
| ለምርታማ ሥራ ስምሪት ተሳትፎ ብቁ ያልሆነ የሰው ኃይል | 2,807,775 | 1,166,315 | 1,641,460 |
| ለሥራ ተሳትፎ ብቁ የሆነው የሰው ኃይል በመቶኛ | 57.9 | 62.9 | 53.6 |
| ለሥራ ተሳትፎ ብቁ ያልሆነው የሰው ኃይል በመቶኛ | 42.1 | 37.1 | 46.4 |
| ለሥራ ከደረሱት መካከል በምርታማ ሥራ ላይ የተሰማሩት የሰው ኃይል ብዛት በመቶኛ | 42.8 | 51.8 | 34.8 |
| በሀገሪቱ ጠቅላላ ከተማ ያሉ የሥራ አጦች ብዛት | 1,010,375 | 345,901 | 664,474 |
| የሥራ አጥነት መጠን በመቶኛ | 26.1 | 17.5 | 35.1 |
| ዕድሜያቸው አስር እና ከዚያ በላይ የሆናቸው በምርታማ ሥራ ላይ የተሰማሩት | 2,858,027 | 1,628,523 | 1,229,504 |
| በጅምላና ችርቻሮ ንግድ የሥራ ዘርፍ | 23.4 | 12.4 | 11.0 |
| በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ የተሰማሩት በመቶኛ | 15.4 | 8.0 | 7.4 |
| መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ | 1,138,781 | 559,378 | 579,405 |

- *በከተሞች ተከታታይ የሥራ ሥምሪት የመጀመሪያው ዙር ጥናት ውጤት መጋቢት 1996 ዓ.ም ማዕከላዊ ስታቲስቲክ ባለሥልጣን*